# የዲሲፒኤስ የነዋሪነት ማረጋገጫ መመሪያዎች

በየዓመቱ፣ ዲሲፒኤስ የእያንዳንዱን ተማሪ በዲሲ ነዋሪነትን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል። የሚከተሉት መመሪያዎች፣ ለ 2011 – 2012 የትምህርት ዓመት፣ አጠቃላይ ሁለ አቀፍ የነዋሪነት ማረጋገጫ ገጽታዎችን ያቀርባሉ።

**የነዋሪነት ማረጋገጫ ዋና ጭብጦች፤**

- የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ነዋሪዎች ብቻ ናቸው በዲስትሪክት ነፃ የሆነ የሕዝብ ትምህርት ማግኘት የሚችሉት
- በአአሁኑ ጊዜ የሚሠራበት የነዋሪነት ማረጋገጫው ደንቦች፣ የዲስትሪክቱ ነዋሪዎች ብቻ የሆኑና በዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ገንዘብ እንዳይከፍሉ ለማድረግ የተቀየሱ ናቸው።

**የአሠራር ቅደም ተከተሎች፤**

- ትምህርት ቤቶች የነዋሪነት ማረጋገጫዎችን ፎቶ ኮፒ እንዲያደርጉ አይጠበቅም። ይሁን እንጂ የነዋሪነት ማረጋገጫው ቅጽ በተማሪዎች የትምህርት ቤት የምዝገባ ቆጠራ ምርመራ ወቅት አጠያያቂ ሁኔታዎች ከገጠመ፣ ትምህርት ቤቶች ምናልባት ማረጋገጫው ከሌላቸው ፎቶ ኮፒ ቅጂዎችን እንዲ ያቀርቡ ይጠበቃል፤
- *አንድን ተማሪ የሚያስመዘግበው ሰው ነዋሪነት ለማረጋገጥ የሚያቀርባቸው ማስረጃዎች ዋና ሰነዶች (original documents) መሆን አለባቸው፤*
- ዓመታዊ የነዋሪነት ማረጋገጫው ጥቅምት (October) 5, 2011 ወይም ምዝገባ በተካሄደበት 10 ቀናት ውስጥ መካሄድ አለበት፤
- ዓመታዊው የነዋሪነት ማረጋገጫው፣ በተያዘው ትምህርት ውስጥ ከሚያዚያ (April) 1 በፊት ቀድሞ (ከጥቅምት (Oct). 5, 2011 ይጠናቀቃል አይከናወንም፤
- የነዋሪነት ማረጋገጥ ደረጃ፣ በክፍል (1) ወይም (2) ላይ ከዚህ በታች ተመልክቶ በቀረበው መሠረት በአጥጋቢ መረጃዎች አማካይነት በመጠቀም በሚመዘገብበት ትምህርት ቤት መረጋገጥ አለበት፤

## አንድ (1) የነዋሪነት ማረጋገጫ ለማቅረብ አስፈላጊ ሁኔታዎች

| <u>ከሚከተሉት እንዱ ነጥብ፣</u> የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ነዋሪ መሆንን ለማረጋገጥ ብቁ ይሆናል | |
|---|---|
| **የዲሲ ነዋሪነትን ለማረጋገጫ ተቀባይ የሚሆን ነጥብ፤** | **ነጥቦቹም የሚከተሉትን ማሳየት አለባቸው፤** |
| 1. **የደሞዝ መክፍያ ጉራጅ ወረቀት** | ሀ. በ 45 ቀናት ውስጥ የተሰጠ፤<br>ለ. ተማሪውን የሚያስመዘግበው ሰው ስም፤<br>ሐ. በአሁኑ ጊዜ በዲሲ የሚኖሩበት ቤት አድራሻ፣ እና<br>መ. ለተያዘው ዓመት የሥራ ግብር ታክስ ተቀናሽ እየሆነ የሚቆረጥበት ማስረጃ |
| 2. **ከዲሲ ክልል መንግሥት የገንዘብ እርዳታ** ማግኘትን በሚመለከት መንገድ የሚያረጋግጥ፤<br>ሀ. ለችግረኛ ቤተሰቦች (TANF) ጊዜያዊ ድጋፍ መደረግን የሚያ መለከት ጽሑፍ ወይም ማስረጃ ደብዳቤ፤<br>ለ. ለሜዲኬድ የብቁነት ማረጋገጫ ደብዳቤ ወይም ብቁ መሆንን የሚያመለክት በድጋሚ የተሰጠ ማረጋገጫ፤<br>ሐ. ከቤቶች ድርጅት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት የተሰጠና የኃላፊ ሠራተኛውን ስም እና ስልክ ቁጥሩን ጭምር የያዘ የመኖሪያ ቤት ድጋፍ ማስረጃ ደብዳቤ፣ ወይም<br>መ. ከሌላ የዲሲ መንግሥት ፕሮግራም፣ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ማረጋገጫ ወረቀት | ሀ. በአለፉት 12 ወራት የተሰጠ ለመሆኑ ቀኑን የሚያሳይ ማስረጃ<br>ለ. ተማሪውን የሚያስመዘግበው ሰው ስም እና<br>ሐ. በአሁኑ ጊዜ በዲሲ የሚኖርበት ቤት አድራሻ እና |
| 3. ተጨማሪ ዐመታዊ የገቢ ዋስትና ማረጋገጫ ማስታወቂያ | ሀ. የተሰጠበት ጊዜ በአለፉት 12 ወራት መሆኑን የሚያመለክት ማረጋገጫ<br>ለ. ተማሪውን የሚያስመዘግበው ሰው ስም እና<br>ሐ. በአሁኑ ጊዜ በዲሲ የሚኖርበት ቤት አድራሻ |
| 4. ከታክስ ክፍያ ነጻ መሆንን የሚያመለክት ቅጽ በዲሲ የታክስ ቀረጥ ገቢ መሥሪያ ቤት የተረጋገጠ ማስረጃ | ሀ. ተማሪውን የሚያስመዘግበው ሰው ስም<br>ለ. ለአለፈው የታክስ ዘመን ለዲሲ የታክስ ቀረጥ ገቢ የተደረገበት ማስረጃና፣<br>ሐ.በአሁኑ ጊዜ በዲሲ የሚኖርበት ቤት አድራሻ |
| 5. ለውትድርና አገልግሎት መኖሪያ ቤት እንዲሰጥ የተፈቀደበት ማዘዣ እና ማስረጃዎች <u>እና</u> ወይም የ **DEERS ወረቀት*** | ሀ. የተማሪው ስም<br>ለ. በአሁኑ ጊዜ በዲሲ የሚኖርበት ቤት አድራሻ |

| | |
|---|---|
| 6. አንድ ልጅ **በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ጥበቃ ሥር ለመኖሩ የሚያረጋግጥ የፍርድ ቤት ማዘዣ** | ሀ. የተማሪው ስም |
| 7. **የኤምባሲ ደብዳቤ** | ሀ. በተያዘው የትምህርት ዓመት ሚያዚያ (April) 1 ቀን የተሰጠ፣<br>ለ. ተማሪውን የሚያስመዘግበው ሰው ስም፣<br>ሐ. ሕጋዊ ማኅተም፣ እና<br>መ. ልጁን የሚያስመዘግበው ሰውና ተማሪው ጭምር ዲሲ በሚገኝ በኤምባሲ ንብረት በዲሲ አድራሻ በሚገኝ ውስጥ መኖራቸውን የሚመለከት የጽሑፍ ማረጋገጫ |

የዲሲ ነዋሪነትን ለማረጋገጫነት ተግባር ፣ የሚከተሉት ነገሮች በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የግል ገቢ ቀረጥ ለመክፈሉ ማረጋገጫ ተደርጎ <u>**አይወሰድም።**</u> እነዚህም (1) W-2 form (ቅጽ)፣ (2) a federal income tax return (የፌድራል የገቢ ቀረጥ ተመላሽ የተደረገበት ማስረጃ)፣ ወይም (3) a District income tax return (የዲስትሪክት የገቢቀርጥ ተመላሽ ማስረጃ) (በዲሲ የታክስና የቀረጥ ጽሕፈት ቤት የሚረጋገ ረጋግጠው ካልሆነ በስተቀር)።

በዲሲ ነዋሪነትን ማረጋገጥ ተግባር በተመለከተ፣ የሚከተሉት ነገሮች ከዲሲ አስተዳደር የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግ መሆኑን ለማሳየት ማስረጃ ሆነው ሊቀርቡ <u>**አይችሉም።**</u> (1) የ TANF መታወቂያ ካርድ፣ (2) የ ሜዲኬይድ መታወቂያ ካርድ፣ (3) በዲስትሪክቱ ቀጣሪ ከሆነ ድርጅት መታወቂያ ካርድ፣ (የዲሲ መንግሥት ጭምር)፣ ወይም (4) በዲስትሪክቱ ነዋሪ ከሆነ ሰው የድጋፍ ደብዳቤ።

*የ DEERS ነጥቦች የተገኙት ከ MPF መሠረታዊ የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት ነው። የ DEERS ነጥቦች የጥገኞችን ስም እንጂ የአሁኑን አድራሻ የማያሳይ ከሆነ፣ ከቤቶች አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ደብዳቤ ጋር ሊቀናጅ ይችላል።

**ነዋሪነትን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሁኔታዎች** (**አማራጭ 2**)

| <u>**በዚህ ገጽ ጀርባ የሰፈሩት የሌሉ ከሆነ፣ ከዚህ በታች ከሰፈሩት (2) ሁለት ነጥቦች**</u> **በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ነዋሪ መሆንን ለማረጋገጥ አጥጋቢ ማስረጃዎች ይሆናሉ። በእያንዳንዱ በሚቀርቡ ሁኔታዎች የሚቀርበው ስም እና አድራሻ አንድ መሆን አለባቸው።** | |
|---|---|
| **የዲሲ ነዋሪነትን ለማረጋገጫ ብቁ ሆነው የሚወሰዱ ሁኔታ፤** | **የሚከተሉትን ዝርዝር ሁኔታዎቹ ማሳየት አለባቸው፤** |
| 1. ቀኑ ያላለፈበት **ዲሲ የተሽከርካሪ ማስመዝገቢያ** | ሀ. ተማሪውን የሚያስመዘግበው ሰው ስም እና<br>ለ. በአሁኑ ጊዜ በዲሲ የመኖሪያ አድራሻ |
| 2. ቀኑ ያላለፈበት **ያከራይ ወይም የተከራይ ውል** ማስረጃ | ሀ.ተማሪውን የሚያስመዘግበው ሰው ስም<br>ለ. ባሁኑ ጊዜ በዲሲ የመኖሪያ አድራሻ <u>እና</u><br>ሐ.ባለፍት ሁለት (**2**) ወራት የቤት ኪራይ መክፈሉን የሚያረጋግጥ |
| 3. ቀኑ ያላለፈበት **የዲሲ የሞተር ተሽከርካሪ መለማመጃ ፈቃድ** ወይም ሕጋዊነት ያለው የመንጃ ፍቃድ ያልሆነ ሌላ መታወቂያ | ሀ.ተማሪውን የሚያስመዘግበው ሰው ስምና<br>ለ. በአሁኑ ጊዜ በዲሲ የመኖሪያ አድራሻ |
| 4. **አንድ የፍጆታ መክፈያ ወረቀት** (ማለትም የጋዝ፣ የኤሌትሪክ እና የውኃ ፍጆታ መክፈያ ወረቀት ብቻ ተቀባይነት ይኖራቸዋል፤ | ሀ. ተማሪውን የሚያስመዘግበው ሰው ስም<br>ለ. ባሁኑ ጊዜ በዲሲ የመኖሪያ አድራሻ <u>እና</u><br>ሐ. ባለፉት ሁለት (2) ወራት፣ ለጋዝ፣ ለመብራት፣ ለውኃ ለመሳሰሉት ፍጆታዎች የአገልግሎት ሂሳብ የተከፈለበት ማስረጃ ወይም የተሰ ረዙ ቼኮች |

ለዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ ተግባር የሚከተሉት ሁኔታዎች ለዲሲ ለሞተርና ለተሽከርካሪ የማስመዝገቢያነት ወይም የተሽከርካሪነት የፍቃድ ማስረጃ ምትክ ሆነው ሊቀርቡ (**1**) የተሽኸርካሪ ባለቤትነት ማስረጃ፣ ወይም (**2**) በተሽከርካሪ ኢንሹራንስ፣ ምትክ ሆነው ሊቀርቡ <u>**አይችሉም።**</u>

ለዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ ተግባር የሚከተሉት ሁኔታዎች በ (**1**) የስልክ ሂሳብ መክፈያ፣ ወይም (**2**) የኬብል የሂሳብ ክፍያ የፍጆታ ክፍያ ማስረጃ ሆነው ሊቀርቡ <u>**አይችሉም።**</u>

በነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጽ ላይ እና በዚህም ላይ ብቻ ያሉት መመሪያዎች ለዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ ተቀባይ ይሆናሉ። ምንም እንኳን አንድ ወላጅ ወይም ተንከ ባካቢ ሌሎች ዐይነት ማስረጃዎችን ማቅረብ የሚችሉ ቢሆንም <u>ተገቢ ማስረጃ ሆነው ሊወሰዱ አይችሉም።</u>